# የሳምባ ቲቢ በሽታ

## የበሽታ መመርመሪያ እና ክሊኒካዊ ሙከራዎች




**የበለጠ መረጃ**
በውስጠኛው ክፍል ያግኙ

የቲቢ በሽታን ስርጭት አዲስ የምርመራ ዘዴ በመጠቀም መከላከል







SeroSelectTB


ይገርማል፥ እዚህ የምታደርጉት ነገር በጣም ጠቃሚ ነው። ቲቢ በጣም አስቀያሚ ህመም ነው። ለማስቆም ከተቻለ ደስታዬ ወደር የለውም።
የክሊኒካል ሙከራ ጣቢያ
አዎን እኔም እንደዛው።


ቲቢ የሚባለው ህመም ከአንድ ታማሚ ከሆነ ግለሰብ ወደ ሌላ በሚተላለፍ ባክቴሪያ አማካይነት የሚፈጠር ህመም ነው።


ቲቢ ከሚከተሉት አጋጣሚዎች በማናቸውም ቢሆን በአየር አማካይነት ይተላለፋል፡
ahem-ahem.......a-chooo.......bla-bla-bla......ptooie.......tra-la-la
በመሣል
በማውራት
በማዜም
በማስነጠስ
በአክታ


በአንዳንድ እንደ እኛ ባሉ አገራት ውስጥ፥ ቲቢ በጣም ትልቅ ችግር ነው።


በ2017 እ.ኤ.አ. በቲቢ ምክንያት የሞቱ ሰዎች 1.6 ሚሊዮን ያህል ሲሆኑ ወደ10 ሚሊዮን የሚሆኑ ደግሞ ታምመዋል
1 600 000


ሰዎች ከዚህ በላይ
በቲቢ ምክንያት
ለህመም እንዳይዳረጉ
እንፈልጋለን፤ ደግሞም
ለዚህም ነው እንደዚህ
ዓይነት በሆኑ የአካባቢ
ጤና ማዕከላት
የሚያገለግል አዲስ
የመመርመሪያ ዘዴ
የሚያስፈልገን።



በእንደዚህ ዓይነት የጤና አገልግሎት
መስጫ ሊሠራበት የሚችል የተሻለ
የሆነ የመመርመሪያ ዘዴ ማግኘት
ብንችል በርካታ ሰዎች የቲቢ
መድሃኒትን በአንድ ጊዜ አግኝተው
ሊያገግሙ ይችላሉ።



ይህማ ይደንቃል!
በእነዚህ ሙከራዎች
ውስጥ የሚሳተፈው
ማን ነው?


ሣል ኖሮበት ወደዚህ
የጤና አገልግሎት መስጫ
የሚመጣ ማንም ሰው ቢኖር
ይህንን ሙከራ እንዲቀላቀል
እንጋብዛለን። ምናልባት
ማንም ሰው ሊቀላቀል
ቢፈቅድ፥ በገዛ ፍቃዱ ነው
የሚሆነው። የሙከራውን
ሁኔታ በሚመለከት ሙሉ
ማብራሪያ ከተሰጣቸው
እና መሳተፋቸው ምን
ሊያስከትል እንደሚችል
ከተገነዘቡ በኋላ ብቻ
ነው የሚቀላቀሉት።
በማንኛውም ጊዜ ላይ
ከሙከራው መውጣት
ይችላሉ።


እሺ። እነዚህ
ሙከራዎች
የሚከናወኑት
የት ነው?


እነዚህ ሙከራዎች በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ቢሆንም፥ ልክ እንደ እኛ
ማህበረሰብ ባሉ ቲቢ በብዛት በሚገኝባቸው አከባቢዎች እነዚህን
ሙከራዎች ማድረግ በተለየ ሁኔታ ጠቃሚ ነው።


ሊሠራበት የሚችል አዲስ መመርመሪያ ዘዴ ቶሎ ብለን ማግኘት ከቻልን በዓለም ዙሪያ የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ለህመም ከመዳረጉ በፊት ቲቢን ልናስቆም እንችላለን።
ለመርዳት ብችል ደስ ይለኛል! ቲቢን የመመርመሪያ ዘዴ ለማግኘት በሚደረገው ምርምር ውስጥ ተሳታፊ ብሆን ለእኔ እጅግ ድንቅ ነው፡፡
የክሊኒካል ሙከራ
በዚህ የሙከራ ሒደት በመሳተፌ የሚያጋጥመኝ አደጋ ይኖር ይሆንን?
ምንም አደጋ የለውም። ዳሩ ግን በሙከራው ሒደት በመሳተፍዎ ምክንያት እኛ አነስተኛ የደም ናሙና እንወስዳለን።
አዲሱን የመመርመሪያ ዘዴ በመጠቀም የእርስዎነ ደም እንመምራለን፡ ፡ የዚህ ምርመራ ውጤት ፖዘቲቭ ሆኖ ከተገኘ ዛሬውኑ ወደ አቅራቢያችን ክሊኒክ እንዲሄዱ እንጠይቅዎታለን። በክሊኒኩም አክታዎ ተመርምሮ ቲቢ ከተገኘብዎት ደግሞ መድሃኒቶች ይሰጡዎታል።
ምርምሩን ማድረግ እና በምችለው አቅም እኔ እርዳታ ማድረጌ ለምን አስፈላጊ ሆኖ እንደተገኘ አሁን ገና ነው የገባኝ። በእንደ እነዚህ ዓይነት አገልግሎት መስጫዎች ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አዲስ የቲቢ መመርመሪያ ዘዴ ቢኖር ተጨማሪ ሰዎች በህመሙ ከመያዝ እንዲከላከሉ ያስችላል።







ይህ የማህበረሰብ ተሳትፎ መረጃ አይኤቪአይ  ያዘጋጀው ላይ ተንተርሶ ለሚፈለገው ዓላማ ተስተካክሎ የቀረበ ነው።

iavi

# ማስታወሻ

**የSeroSelectTB ኮንሶርቲየም ተልዕኮ ፈጣን የሆኑ እና አቅምን ያገናዘቡ የቲቢ መመርመሪያ ዘዴዎችነ ለማዘጋጀት ነው::**

